# የሬስቶራንት እድሳት የገንዘብ ድጋፍ

የአሜሪካ የማዳን ዕቅድ ሕግ ፣ ሬስቶራንቶች እና ሌሎች ብቁ የሆኑ የንግድ ተቋማት በራቸው ክፍት እንዲሆኑ ለማገዝ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የምግብ ቤት እድሳት ፈንድ (Restaurant Revitalization Fund, RRF) አቋቁሟል ፕሮግራሙ ሬስቶራንቶችን በወረርሽኙ ምክንያት ያጡትን የገቢ ኪሳራ ጋር እኩል የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ፣ በአንድ የንግድ ሥራ እስከ $10 ሚሊዮን ዶላር እና በአካላዊ ቦታዎች ከ $5 ሚሊዮን ዶላር የማይበልጥ ድጋፍን ያቀርባል። የድጋፉ ተቀባዮች ገንዘብ ለብቁ አጠቃቀሞች እስከ መጋቢት 11፣ 2023 ድረስ ጥቅም ላይ እስከዋሉ ድረስ የገንዘብ ድጋፉን መልሰው እንዲከፍሉ አይጠየቁም።

ለበለጠ መረጃ www.sba.gov/restaurantsን ይጎብኙ።

## ማነው ማመልከት የሚችለው

ማንኛውንም በወረርሽኙ ምክንያት የገቢ ማጣት ያጋጠማቸው ብቁ አካላት፣ ይህም የሚያካትተው፡-

- ሬስቶራንቶች
- በቋም የሚበላባቸው ምግብ መሸጫዎች ፣ የምግብ መሸጫ መኪናዎች ፣ የምግብ መሸጫ ጋሪዎች
- የምግብ አቅራቢዎች
- ቡና ቤቶች ፣ ሳሎኖች ፣ ላውንጆች ፣ መጠጫ ቤቶች
- የማክሳስ እና ከአልኮል ነጻ የሆኑ መጠጦች ባር
- የተፈቀደላቸው ተቋማት ወይም ህብረተሰቡ ሊሚቀምስበት የሚችልበት ፣ የናሙና ወይም ምርቶችን የሚገዛበት የመጠጥ አልኮል አምራች ግቢ
- ደቦ ቤቶች*
- መጠጥ አጥምቂዎች ፣ የመቅመሻ ክፍሎች ፣ የቢራ መቅጃ ክፍሎች*
- የቢራ ፋብሪካዎች እና/ወይም ጥቃቅን የቢራ ፋቢሪካዎች*
- የዋይን ወይም የአረቄ ማጥመቂያዎች*
- መጠለያዎች*

** በቦታው ላይ ለህዝብ የሚደረገው ሽያጭ ቢያንስ የጠቅላላ ደረሰኞችን33% ያካተተ ከሆነ*

## እንዴት እና መቼ ማመልከት እንደሚቻል

በ SBA እውቅና ባለው የሽያጭ ምግብ ቤት ባልደረባዎች በኩል ወይም በቀጥታ በSBA በኩል በሚመጣው የመስመር ላይ የመተግበሪያውን መግቢያ በhttps://restaurants.sba.gov ማግኘት ይችላሉ።

SBA ማመልከቻው ክፍት ሲሆን በኤሜል እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ በኩል ያሳውቃል። የኢሜል ማንቂያዎችን ላይ በ www.sba.gov/updates ወይም የምህበራዊ ሚዲይ አካዎንቶቻችንን መመዝገብ ወይም www.sba.gov/social-media ማግኘት ይችላሉ።

ሲያመለክቱ ተጨማሪ መረጃ ሊጠየቅ ይችላል። ሙሉ ዝርዝሩን በ www.sba.gov/restaurantsይመልከቱ።

## በማመልከቻዎ ላይ እገዛ ለማግኘት

ማመልከቻዎን ለማዘግጀት ድጋፍ ከፈላጉ ፣ የሚከተሉትን ማግኘት ይችላሉ፡-

- የጥሪ ማዕከላት ድጋፍ፡- 1-844-279-8898 (ሰዓታት፡- ከሰኞ-አርብ 8am-8pm ET)
- የSBA ዎ ዲስትሪክቱ ጽፈት ቤትን በ www.sba.gov/local-assistance
- የናሙና ማመልከቻ ቅጽ እንዲሁም ዝርዝር የፕሮግራሙ መመሪያዎች በበርካታ ቋንቋዎች በwww.sba.gov/restaurantsላይ ይገኛሉ።